

# ሲኦል እውን ናት፥ እኔ እዛ ሄጄ ነበር!

## በ ጄኒፈር ፔሬዝ

*በክርስቲያን ቤት ውስጥ ያደገች የ15 ዓመት ሴት ልጅ ምስክርነት፣ እርሷ ከዛ በመንገዷ ወደ ኋላ አፈገፈገች፣ ከመጠን በላይ አደንዛዥ እጽ ተጠቅማ፣ እየሞተች፣ እና ወደ ሲኦል እየተላከች እራሷን አገኘችው። እንደ መታደል ሆኖ፣ እርሷ ሁለተኛ እድልና ተመልሳ የጠፉትን፣ ወደ ኋላ ያፈገፈጉትን፣ እና ለብ ያሉትን በአስቸኳይ መልእክት እንድታስጠነቅቅ አገልግሎት ተሰጣት።*

*(ከተቀረጸ ድምፅ በጽሑፍ ተፃፈ)*

**እግዚአብሔር** ይባርካችሁ ወንድሞችና እህቶች፥ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ከፍታችሁ ወደ ትንቢተ ኢዩኤል 2:28 እንድትገልጡ እፈልጋለሁ። *"ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፣ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤"*

ስሜ ጄኒፈር ፔሬዝ ነው እድሜዬም 15 ዓመታት ነው። እንደ እኔ ላለ ለታዳጊ ወደ እናንተ መጥቶ የራሴን ጥፋቶች ማገናዘብ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በ**መንፈስ ቅዱስ** እርዳታ፥ እርሱ ይረዳኛል፥ እና የሚያስፈልገኝን ጥንካሬ ይሰጠኛል። ከሁሉ አስቀድሜ ይህ **ለጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ** ውዳሴና ክብር ነው ለማለት እፈልጋለሁ። አንዳች ህግ ወይም አንዳች አዲስ ህግ ፈጥሬ ለማለት አልፈልግም፣ እኔ ያየሁትን፣ የሰማሁትን፣ እና የተሰማኝን ብቻ ልነግራችሁ ነው።

ስለ ወላጆቼ ጥቂት ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ወላጆቼ ክርስቲያኖች ናቸው። እነርሱ ሁል ጊዜ መልካም ምሳሌዎችን፣ እና የ**ጌታ**ን መንገድ አስተምረውኛል። ከሦስት ዓመታት በፊት ከወንድም ኒኪ ክሩዝ (Nicky Cruze) ጋር **ጌታ**ን ስቀበል ክርስቲያን ሆንሁኝ። ለሁለት ዓመታት በ**ጌታ** መንገዶች ተጓዝሁ። ነገር ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርትን ስጀምር፥ አመጸኛ መሆን ጀመርሁና የ**ጌታ**ን መንገድ ተውኩኝ። እኔ ለወላጆቼ አመጸኛ ነበርሁ እና ወደ አደንዛዥ እፆች ውስጥ ገባሁ። እነዛን ነገሮች እንዳደርግ ጓደኞቼ አስተማሩኝ።

ክርስትያን እንደሆንሁኝ እና ጓደኞቼ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ አመጣቸዋለሁ ብዬ አስብ ነበር። ነገር ግን በዛ ፈንታ፣ እነሱ ወደኋላ አውጥተው ዓለም ውስጥ አመጡኝ። ለወላጆቼ አመጸኛ ሆኜ ነበረ፥ እና እነርሱ በቃ ታዳጊዎች የሚያልፉበት አንድ ነገር ነው ብለው አስበው ነበር። ነገር ግን በእርግጥ፥ አደንዛዥ እፆቹ እንዳደርግ ያደረጉኝ ነበር። ክፉ መናፍስት ወደ ውስጤ ገቡ፥ የዛኔ ነበር ለቤተሰዎቼ አመጸኛ የሆንኩት። እነርሱ በኔ ላይ ጥብቅ ስለነበሩ የትም ቦታ እንድወጣ በፍጹም አይፈቅዱልኝም፥ አንድ ሌሊት እንኳ በጓደኛ ቤት እንዳሳልፍ አይፈቅዱልኝም። ሁል ጊዜ ሁሉንም ነገር ሹልክ ብዬ በመውጣት ወይም እነርሱ ሳያውቁ ማድረግ ነበረብኝ። ከትምህርት ቤት እኮበልል ነበር (ትምህርት ቤት ሳልሄድ እቀር ነበር)። ልማዴን ለመጠበቅ ብቻ፥ በችግር እንኳ ትምህርት ቤት እሄድ ነበር (ልማዴን ለመጠበቅ ብቻ በችግር ነበር ትምህርት ቤት የምሄደው)። ሱሰኛ የመሆን ጫፍ ላይ ነበርሁ፥ ነገር ግን **ጌታ** ከዛ ሁሉ አወጣኝ። እንዳልሁት፣ እኔ ክርስትያን ነበርሁ።

ምስክርነቴ በሜይ 2፣ 1997 ይጀምራል። አንድ ጓደኛ ነበረኝ፥ እኛ ጓደኛሞች ብቻ ነበርን፥ ከዛ ተጨማሪ ምንም የለም፥ እርሱም ያን ያውቀዋል። እያወቅሁት ነው ብዬ አስብ ነበር፥ በእርግጡ ግን እሱ ማን እንደነበረ የእውነት አላውቀውም ነበር። በዛ ሌሊት፥ እሱ ጠራኝና መውጣት እችል እንደሆን ጠየቀኝ። ወላጆቼ ቤት አልነበሩም። እነርሱ በጸሎት ስብሰባ ላይ ነበሩ፥ እንደ ሁል ጊዜ አርብ አርብ። ህመም ስለተሰማኝ እቤት መቆየት እንደምፈልግ ነገርኳቸው። በዛ ምሽት ከተለየ ጓደኛ ጋር ወደ ውጭ ለመውጣት እቅድ ነበረኝ፥ ነገር ግን ወላጆቼ እንድሄድ ስላልፈቀዱልኝ በእነርሱ ላይ በጣም ተቆጥቼም ደግሞ ነበር። ስለዚህ ቤት ውስጥ ለመቆየት ጠየቅሁ፥ እነርሱም ፈቀዱልኝ። እነርሱ ወደ ጸሎት ስብሰባ ሲሄዱ ጓደኛዬ ደወለልኝ። እሱም እንዲህ አለ፦ *"ሌላው ሁሉም ሰው እየወጣ ሳለ አንቺ ለምንድን ነው የማትወጪው?"* እኔም ለራሴ እንዲህ አልሁ፦ *"ለወላጆቼ አለመታዘዝ አልፈልግም። ነገር ግን ምናልባት ሹልክ ብዬ ብወጣ ወላጆቼ በፍጹም አያውቁም"*፥ ስለዚህ ያንን ነው ያደረግሁት።

በዛ ሌሊት ወላጆቼ እቤት ሲደርሱ ተኙ። እኔ ሹልክ ብዬ ለመውጣት ተዘጋጅቼ ስለነበረ ጓደኛዬን ደወልኩለትና በጎዳናዬ መታጠፊያ ጠርዝ ላይ እንዲጠብቀኝ ነገርሁት። ወላጆቼን ሊቀሰቅስና ሁሉንም ነገር ሊያበላሽ ስለሚችል በቤቴ አጠገብ (በኩል) እንዳያልፍ ነገርሁት። ስለዚህ ከብርድልብሴ በታች ትራሶቼን አስቀመጥሁና በመስኮቴ በኩል ዘለልሁ። እኔ የምኖረው በባለ ሁለት ፎቅ ቤት ውስጥ ነው፥ እና የቤቴ ሁሉም መስኮቶች ብሎኖች አሏቸው። ነገር ግን ወላጆቼ ስላመኑኝ የኔ መስኮት ምንም ብሎኖች አልነበሩትም። ስለዚህ የወላጆቼን መተማመን እንደ ጥቅም ወሰድሁት። እኔ በሁለተኛው ፎቅ ውስጥ ስለምኖር ከጣሪያው ላይ ዘለልሁና መሬት ላይ አረፍሁ። **ጌታ** ሁሉንም ነገር አቅዶ ነበር፥ ምክንያቱም እኔ እግሬን ልሰብር እችል፥ እና **ጌታ** ለኔ ያቀደልኝን ሁሉንም ያ ያቆመው ነበር።

በመንገዱ ወደታች ተራመድሁ፥ ጓደኛዬም እዛ ነበር። መኪናው ውስጥ ስገባ ግን፥ 3 ወንዶችና ሌላ አንድ ሴት አየሁ። ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፦ *"እኔ አንዳች አላደርግም፣ ዪ (አዎ)፣ እጦዛለሁ (I will get high)፣ አደንዛዥ እፆችን እጠቀማለሁ፣ እጠጣለሁ።"* ነገር ግን እዛ ሌሎች 3 ወንዶችና አንዲት ሴት ሲኖሩ፥ ሊጠቀሙብኝ ይችላሉ ብዬ ፈራሁ። ነገር ግን መኪናው ውስጥ ገባሁና ሄድን። በፊት፥ ከጓደኛዬ ጋር በስልክ ስናወራ፥ በፅኑ ፍላጎት በከተማው ዙሪያ ብቻ እንዘራለን ብሎ ነበር። እኔም እንዲህ አልሁ፦ *"እሺ ያ የሚያስደስት ይመስላል"*፥ ለዛ ነው የሄድሁት። ወደ ሞቴል (ትንንሽ ክፍሎች ያሉት በመንገድ ዳር የሚገኝ ሆቴል) ሊወስደኝ ነው ብዬ በፍፁም አላሰብሁም ነበር። እኔን እዛ ነበር የወሰዱኝ።

እዛ እንደደረስን፥ የሞቴሉ በሆነ የልብስ ንፅህና አገልግሎት በሚሰጥበት በአንድ ክፍል አወረዱኝ። እነሱ እዛ እንድንጠብቅ ነገሩን፥ እነሱ ሌላ ጓደኛ ይዘን ልንመጣ ነው አሉ። እኔም እሺ አልሁ፥ ነገር ግን ቤት ሊከራዩ እንደሄዱ እገምታለሁ። እነሱም ተመልሰው መጡና እኛን ወሰዱን፥ ወደዛም ክፍል ወሰዱን። እነሱም እንዲህ አሉ፦ *"አትጨነቂ፥ መተማመንሽን በእኛ አኑሪ! እኛ አንዳች አናደርግም፥ ሌላኛው ጓደኛችን እስኪመጣ ድረስ ልንጠብቅ ብቻ ነው፥ እና ከዛ ሁላችንም በአንድ ላይ እንሄዳለን"*። ስለዚህ መተማመኔን በጓደኞቼ ላይ አደረግሁ፥ እነሱ በፍፁም አይጎዱኝም ብዬ አሰብሁ፥ በእርግጥ ግን ጓደኞቼ ማን እንደነበሩ የእውነት አላውቅም ነበር።

በመጀመሪያ፥ እያወራን ብቻ ስለነበር እንዲህ አልሁኝ፦ *"እየጠበቅን ሳለ የሚጠጣ አንዳንድ ነገር ለምን አናገኝም?"* ስለዚህ ጓደኛዬና እኔ ከክፍሉ ወጣንና ከሞቴሉ ፊት ለፊት ወዳለ ወደ አንድ ትንሽ ሬስቶራንት ተጓዝን። ሦስት ስፕራይት ገዛንና ተመልሰን ወደ ክፍሉ ተራመድን። እነሱ ስፕራይቱን ወደ ኩባያዎች ውስጥ መቅዳት ጀመሩ። በመጠጤ ውስጥ አንዳች ነገር ሊጨምሩ ነው፣ ወይም አንዳች ያደርጉብኛል ብዬ እንዳስብ የሚያደርገኝ የሚያጠራጥር የሚመስል ቦርሳ ወይም አንዳች አላመጡም ነበር። ሁሉም ንፁህ ይመስላል።

እኔም ፀጉሬን ለማስተካከልና የሴት ነገሮችን ለማድረግ ወደ መታጠቢያ ክፍል ሄድሁኝ፣ እና ወጥቼ ስመጣ ኩባያዬ ተዘጋጅቶ ነበር። እኔም አንድ እንጆሪ ማስቲካ አፌ ውስጥ ከተትሁና፥ ስፕራይቴ ነው ብዬ አስብ የነበረውን ጠጣሁ። ከዚህ በኋላ ምን እንደሆነ አላውቅም።

ነገር ግን ማየት ስችል፣ መንፈሴ ከሰውነቴ ውስጥ ሲወጣ ተሰማኝ። ሆስፒታል ውስጥ ነበርሁኝ፥ ዶክተሮችንና ነርሶችን በዙሪያዬ አየሁ። ከሰውነቴ ወጥቼ ሳለሁ፣ ሰውነቴ (አካሌ) አልጋ ላይ ሆኖ አየሁ። በመስታወት ውስጥ ራሳችሁን እንዴት እንደምትመለከቱ ታውቃላችሁ፥ አንድ ነፀብራቅ ታያላችሁ። እኔ ግን የራሴን ነፀብራቅ አላየሁም፥ የራሴ አካል አልጋ ላይ ሆኖ አየሁ። ስዞር፥ ቀይ የለበሱ ሁለት ሰዎች ነበሩ፣ *"በእኛ መንገድ ነዪ"* እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ክንዴን ያዙኝ።

እነርሱ ወደ አንድ ቦታ ወሰዱኝ፥ እና የት እንደነበርሁ ስመለከት፥ ገነት ነበረ!። ያየሁት የመጀመሪያ ነገር አንድ ታላቅ ትልቅ ግድግዳ ነበረ። ነጭ ነበረ እና በርቀት ተዘርግቶ ስለነበረ መጨረሻ የለውም ነበረ። በግድግዳው መሐል ላይ አንድ ረጅም በር ነበረ፥ ነገር ግን ተዘግቶ ነበር።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፥ ሙሴ ስለ ቤተ መቅደስ ይናገራል እና የቤተ መቅደሱን ሁኔታዎች ይገልፃል። እኔም ይህን አስታወስሁ፥ ግድግዳውም እንደ ገለፃው እንደሚመስል አየሁ። ከበሩ በቀኝ ጎን፥ አንድ ግዙፍ ወንበር ነበረ፥ እና አንድ አነስተኛ ወንበር በቀኝ በኩል ነበረ። ወንበሮቹም ከወርቅ የተሠሩ ይመስላሉ። በቀኜ በኩል፥ አንድ ግዙፍ ጥቁር በር ነበረ፥ ዙሪያውን በጣም ጨለማ ነበረ፥ እኔ ግን ከእጀታው የተነሣ በር እንደሆነ አውቄ ነበር። አስቀያሚ በር ነበር።

በግራዬ በኩል ግን ገነት ነበረ፥ እዛ ዛፎች፣ በጣም ንፁህ የውኃ ፏፏቴ፣ ሳር ነበሩ። በጣም ሰላማዊ ቦታ ነበረ፥ ነገር ግን እዛ ማንም አልነበረም።

እኔም ተመለከትሁ እና **አብን** (**እግዚአብሔር አብን**) ከፊት ለፊቴ አየሁት። ፊቱን ማየት አልቻልሁም ነበር፥ የእርሱ ክብር በጣም ትልቅ፣ በጣም ብሩህ (ደማቅ) ስለሆነ፥ በራና መንግሥት ሰማይን ሁሉ አበራው። የእርሱ ክብር ሁሉንም ነገር ብሩህ አደረገ። እዛ ምንም ፀሐይ፣ ምንም ጨረቃ፣ ምንም ከዋክብት አልነበሩም፣ እርሱ ብርሃን ነበረ። የእርሱን አካል አላየሁም፥ እና የእርሱ አካል ከ**ወልድ** ጋር ነበረ፥ እነርሱ እርስ በራሳቸው ውስጥ አንድ ነበሩ፣ እነርሱ አንድ ላይ ነበሩ፣ የእነርሱን መለየት ማየት ትችላላችሁ፥ ነገር ግን እነርሱ በሌላኛው ውስጥ አንድ ነበሩ (አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ አንድ ነበሩ)፥ እነርሱ አንድ ላይ ነበሩ።

ከእነርሱ አጠገብ ሁለት መላእክት ነበሩ፣ ገብርኤል እና ሚካኤል። ስማቸውን ያውቅሁበት ምክንያት ስማቸው ግምባራቸው ላይ በወርቅ ተጽፎ ነበረ።

ከ**አብ** ፊት ሳለሁ፥ ቆሻሻ እንደሆንሁ ተሰማኝ! እኔም በጉልበቶቼ ወደቅሁና አለቀስሁ። በራሴ በጣም አፍሬ ነበረ። በራሴ አፍሬ ስለነበረ፥ ፊታቸውን ማየት ብችልም እንኳ ማየት አልፈለግሁም ነበር። ከ**ጌታ** ፊት እዛ እንዳለሁ፥ እርሱ ከመጀመሪያው እስከ አሁን ድረስ ያለውን የህይወቴን ፊልም አሳየኝ። እጅግ ጠቃሚው ክፍል የነበረው እኔ ከዳንሁኝ በኋላ ያደረግኋቸሁ ነገሮች እንደሆኑ እርሱ ነገረኝ። እኔ ክርስቲያን እንደሆንሁኝ ለጓደኞቼ ነግሬያቸዋለሁ፥ ነገር ግን በእርግጥ ፍሬዎቼን አላሳየሁም። የጉዞ መድረሻዬ ወደ ሲኦል ለመሄድ እንደነበረ እርሱ ነገረኝ።

መልአኩ ገብርኤል መጣና ክንዴን ያዘኝ። እርሱ ለማየት እንኳ ወደማልፈልገው ወደዛ አስቀያሚ ጥቁር በር ወሰደኝ። ራሴን ለማቆም ሞከርሁ፥ እኔ ግን በመንፈስ ነበርሁ፥ እና በበሩ ውስጥ አልፈን ሄድን። በበሩ ውስጥ አልፌ እንደገባሁ ዙሪያውን ሁሉ ጨለማ ነበረ፥ ራሴን እንኳ ማየት አልቻልሁም ነበረ። ከዛም እኛ እንደ ሮለር ኮስተር (በጣም በፍጥነት እንደሚምዘገዘግ ባቡር) ወደ ታች መውረድ ጀመርን። ወደ ታች እየወደቅን (እየወረድን) ሳለ በጣም እየሞቀ እየሞቀ ነበር። እኔም ዓይኖቼን ከደንሁ፥ የት እንደነበርን ለማየት አልፈለግሁም።

እንደቆምን፥ ዓይኖቼን ከፈትሁ፥ እኔም በአንድ ታላቅ መንገድ ላይ ቆሜ ነበረ። ወደ የት እንደሚመራ አላውቅም ነበር። ነገር ግን እዛ የተሰማኝ የመጀመሪያው ነገር መጠማት (ጥማት) ነበረ። የእውነት ጠምቶኝ ነበረ! *"ተጠምቻለሁ፣ ተጠምቻለሁ"* በማለት ለመልአኩ መናገሬን ቀጠልሁ። ነገር ግን እርሱ ያልሰማኝ እንኳ ይመስል ነበር። እኔም ማልቀስ ጀመርሁ፥ እና በጉንጮቼ ላይ እንባዎቼ ሲወርዱ፥ እንባዎቼ ሙሉ በሙሉ ይተኑ ነበር። እዛ እንደሚነዱ ጎማዎች የሰልፈር (የድኝ) ሽታ ነበረ። እኔም አፍንጫዬን ለመሸፈን ሞከርሁ፥ ነገር ግን እንደዛ ማድረጌ የበለጠ እንዲብስ አደረገው። ሁሉም 5ቱ የስሜት ህዋሶቼ በጣም ንቁ ነበሩ። ራሴን ለመሸፈን ስሞክር፥ ሰልፈሩን (ድኙን) የበለጠ ማሽተት እችል ነበር። ደግሞ፥ በክንዶቼ ላይ ያሉ እነዛ ትናንሽ ፀጉሮች በቃ ጠፉ። ሁሉም ሙቀት ተሰማኝ፥ በጣም ይሞቅ ነበር።

ዙሪያውን መመልከት ስጀምር፥ ሰዎች በአጋንንት ሲሠቃዩ አየሁ። እዛ እየተሠቃየች ያለች አንድ ሴት ነበረች፥ አንድ ጋኔን እያሠቃያት ነበር። ይህ ጋኔን ራሷን (ጭንቅላቷን) ይቆርጠው ነበረ እና በረጅም ጦሩ ሁሉም ቦታ ይወጋት ነበር። እሱ አይጠነቀቅም ነበር። ዓይኖቿ ውስጥ፣ አካሏ ውስጥ፣ እግሮቿ ውስጥ፣ እጆቿ ውስጥ፥ እሱ አይጠነቀቅም ነበር። ከዛ እሱ ራሷን (ጭንቅላቷን) መልሶ አካሏ ላይ ያስቀምጠው ነበር እና ይወጋትና ይወጋት ነበር። እርሷ በሥቃይ ጩኸቶች ታለቅስ ነበረ።

ከዛ ሌላ ጋኔን አየሁ፥ ይህ ጋኔን ከ21-23 ዓመት እድሜ የሚገመት አንድን ወጣት ሰው እያሠቃየ ነበር። ይህ ሰው በአንገቱ ዙሪያ ሰንሰለት ነበረ፥ እና ከእሳት ጉድጓድ ፊት ለፊት ቆሞ ነበር። ይህ ጋኔን በረጅም ጦር ሁሉም ቦታ ላይ ይወጋው ነበር፣ ዓይኖቹ ውስጥ፣ በየቦታው። ከዛ ጋኔኑ ጸጉሩን ይይዘውና በሰንሰለቶቹ ይህን ሰው ወደ እሳቱ ጉድጓድ ውስጥ ይወረወረው ነበር፥ ከዛ መልሶ ያወጣዋል እና ይወጋውና ይወጋው ነበር። ይህ ያለማቋረጥ ይቀጥል ነበር፥ እና እሱ እዛ ጉድጓድ ውስጥ በሄደ በእያንዳንዱ ጊዜ ጩኸቶቹን መስማት እችል ነበር፣ ነገር ግን ጋኔኑ ሲያወጣው፥ እሱ በሥቃይ ይጮህ ነበር።

ድምፁ በጣም አስከፊ (የሚያሰቅቅ) ስለነበረ ጆሮዎቼን ለመሸፈን ሞከርሁ፥ ነገር ግን አሁንም መስማት እችል ነበር። አሰማሙ የበለጠ ንቁ ሆኖ ነበር።

ሌላ ጋኔን ተመለከትሁ፥ ይህ ጋኔን በጣም አስቀያሚ ነበረ፥ ሌሎቹ ሁለቱ አጋንንትም አስቀያሚ ነበሩ፥ ይህኛው ግን በጣም አስቀያሚ ነበረ። እሱ የብዙ የተለያዩ እንስሳት ባህርይ ነበረው፥ በቃላት ላብራራው እንኳ አልችልም። ዙሪያውን ይሄድና ሰዎችን ያስፈራራል፥ ሰዎቹም የእውነት ይፈራሉ።

ከዛም ሌላ ጋኔን አየሁ፥ ይህኛው ጋኔን ግን ውብ (የሚያምር) ጋኔን ነበረ፥ እሱ እንደ **እግዚአብሔር** መልአክ ይመስላል፣ ነገር ግን አይደለም። በ**እግዚአብሔር** መላእክት እና በአጋንንት መካከል ያለው ልዩነት፥ አጋንንት ስማቸው በግምባራቸው ላይ በወርቅ አልተፃፈም፥ የ**እግዚአብሔር** መላእክት ግን ስማቸው በግምባራቸው ላይ በወርቅ ተጽፎዋል።

ከዛ በኋላ፥ ዞር ብዬ መልአኩ ገብርኤልን ተመለከትሁት፥ እርሱም እየተመለከተ ነበረ። እርሱ ሌሎቹ ሲሠቃዩ ማየት አይፈልግም ብዬ አሰብሁ። ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፦ “*እርሱ ለምንድን ነው እስከ አሁን እዚህ ያለው? እኔ ለመሠቃየት ተራዬን እየጠበቅሁ እዛ ለመሆን የምታሰብ (የምጠበቅ) አይደለሁም እንዴ?*” በጣምም ደግሞ ተጠምቼ ነበር። እኔም ወደ መልአኩ እንዲህ በማለት አለቀስሁ፦ “*ተጠምቻለሁ ተጠምቻለሁ!*” እርሱ ወደ ታች ወደ እኔ ስለተመለከተ የሰማኝ ይመስለኛል፥ እርሱም እንዲህ አለ፦ “***ጌታ*** *አንድ ተጨማሪ እድል ሊሰጥሽ ነው።*”

እርሱ ያን እንዳለ ወዲያውኑ ሁሉም መጠማቴ፣ ሁሉም ሥቃዩ፣ ሁሉም ጎዳቴ ተወ (ጠፋ)። ሰላማዊ ተሰማኝ። ከዛም እርሱ እጄን ያዘና ወደ ላይ ለመነሣት ተዘጋጀን፥ ነገር ግን ወዲያውኑ ስሜ ሲጠራ ሰማሁ፣ “*ጄኒፈር፣ እርጂኝ፣ እርጂኝ!*” ወደ ታች ተመለከትሁ። ማን እንደሆነ ለማየት ፈለግሁ፥ ለማየት ስሞክር ግን የእሳቱ ነበልባል ፊታቸውን ከለለው። ድምፁ እንደ ሴት ድምፅ ይመስላል። እንድረዳት እየፈለገች እጇቿ ብቻ ተዘርግተው ማየት እችል ነበር። እሷን ለመርዳት ልዩ የሆነ ታላቅ መሻትና ፍላጎት ነበረኝ። ስሞክር አልቻልሁም ምክንያቱም እጆቼ በእሷ እጆች ውስጥ ያልፋሉ። እርሷን ለመርዳት እጅግ በጣም ፈለግሁ፥ ነገር ግን አያችሁ፥ እሷ ምንም ተስፋ የላትም። ልረዳት አልቻልሁም።

ከዛም ዙሪያውን ተመለከትሁ እና ጓደኞቼን፣ አውቃቸው የነበሩ ሰዎችን፣ እና ሌሎች ሰዎችን አየሁ። እነሱ የማውቃቸው ይመስላሉ ነገር ግን እነማን እንደነበሩ አላወቅሁም። እኔ ኑሯቸውን አላውቅም፥ ነገር ግን ከትምሕርት ቤቴ የሆኑ ጓደኞችን እዛ ሳይ፥ ያ አሳመመኝ!። ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፦ “*ክርስትያን ነኝ ነገር ግን ወደ ኋላ ተመለስሁ በማለት ለእነርሱ እየሰጠኋቸው የነበረው መጥፎ ምስክርነት ስለ* ***እግዚአብሔር*** *ማወቅ እንዳይፈልጉ ምናልባት አድርጓቸው ይሆናል፥ እና ከ**እግዚአብሔር** ዞር አሉ። እነሱን እዛ ያመጣኋቸው ምንአልባት እኔ እሆናለሁ*”። ያን ነበር ያሰብሁት። በሲኦል ውስጥ ምንም ሰዓት እንደሌለ አየሁ። ምንም ያለፈ፣ አሁን፣ የወደፊት የለም፣ ሁሉም አንድ አይነት ነው፣ እነሱ እዛ ለመሄድ የተወሰኑ ናቸው። ነገር ግን በመጀመሪያ እንዳልሁት አንዳች ህግ መፍጠር አልፈልግም፥ ነገር ግን እዛ ያየኹት ያን ነው። እዛ ያየኋቸው ሰዎች ዛሬም እየኖሩ ናቸው።

ከዛ መልአኩ መልሶ ወደ **እግዚአብሔር** ህልውና ወሰደኝ። ከእርሱ (ከ**እግዚአብሔር**) ፊት ስቆም በጉልበቶቼ ተንበርክኬ እያለቀስሁ እና እያለቀስሁ ነበረ። በራሴ አፍሬ ስለነበር አሁንም ፊቱን ማየት አልፈለግሁም። **ጌታ** ግን ልዩ በሆነ ጣፋጭ ድምፁ እንዲህ አለ፦ “***አፈቅርሻለሁ***” እያዳመጣችሁኝ ያላችሁትን እንደሚያፈቅራችሁ። እርሱ ግን በቀጥታ ለኔ ተናገረው። እርሱን ሳሳዝነው ስላደረግሁት (አድርጌው ስለነበረው) ሁሉም ነገር ይቅርታ እንዳደረገልኝ ተናገረ። **እርሱ** ይቅርታ አደረገልኝ።

**እግዚአብሔር** ተመለከተኝና ብዙ ነገሮችን አሳየኝ። እርሱ ዓለምን አሳየኝ፣ መሬትን። በመሬት ዙሪያ እንደ ያዞን ንጣፍ ለስላሳ የሆነን ነገር አየሁ፥ በዓለም ዙሪያ ነበረ፥ በጣም ለስላሳ ይመስላል፥ እና ያን ለመንካት ልዩ የሆነ መሻት ነበረኝ። ስነካው፥ ስላጠመቀኝ **መንፈስ ቅዱስ** እንደሆነ ተገነዘብሁ፥ እና በሌሎች ልሳኖች መናገር ጀመርሁ።

በዛን ጊዜ፥ ተመለከትሁ እና ብዙ ክፉ መናፍስት ከእኔ ወጡ። ስጦዝና አደንዛዥ እፆችን ስጠቀም አዕምሮዬን ውጥንቅጥ ያደርገዋል እና በሮችን ይከፍታል፣ እነዚህም ክፉ መናፍስት ወደ ውስጤ ይመጣሉ። እነሱ ያሠቃዩኝ ነበር። የምንቀሳቀስበት (ድርጊቶችን የማደርግበት) መንገድ የእውነት እኔ አልነበርሁም፥ በውስጤ የነበሩት ክፉ መናፍስት ነበሩ። **በእግዚአብሔር ቃል** እንዲህ ይላል ቤታችሁ ንፁህ ሲሆን፥ ክፉ መናፍስት ሌሎች 7 ክፉ መናፍስትን በማምጣት ተመልሰው ለመምጣት ይሞክራሉ። ስድን ቤቴ ነጽቶ ነበረ። እኔም እየተጠመቅሁ እያለ እነዚህን ክፉ መናፍስት አየኋቸው፥ እነሱ 7 አላቸው፣ እነዛም ሌሎች 7 አሏቸው፣ እነዛኞቹም ሌሎች 7 ነበሯቸው፣ እናም እኔ ሁሉንም ልቆጥራቸው እንኳ አልቻልሁም! ነገር ግን **ጌታ** ከእነዛ ሁሉ ክፉ መናፍስት አነፃኝ።

እርሱ የወደፊቱንም ደግሞ አሳየኝ። እርሱ ምድርን (መሬትን) እና ነገሮች እንዴት እንደሚሆኑ፣ ሊሆኑ ስላሉ ሁኔታዎች አሳየኝ። ተሰጥቶኝ የነበረው ራእይ (የተሰጠኝ ራእይ) ከአሁን ጀምሮ እስከ መነጠቅ ድረስ ያለ ነው። (ስለ መነጠቅ / ንጥቀት:- **የእግዚአብሔር አብ ልጅና ቃል፣ በመስቀል ላይ የታረደው የእግዚአብሔር አብ በግ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣው፣ በክብር በአባቱም ቀኝ ያለው ጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ** ተመልሶ በእርሱ ያመኑ ከውኃና ከ**መንፈስ ቅዱስ** ዳግም ተወልደውና እንደቃሉና እንደ **ቅዱስ አባቱ እግዚአብሔር አብ ፈቃድ** እየኖሩና የአባቱን ፈቃድ እለት እለት እያደረጉ ያሉትን ቅዱሳን አማኝ ልጆቹን ታዛዥ ክርስቲያኖችን ከታላቁ መከራ በፊት ወደ ቅዱስ ሰማያዊ መንግሥቱ የሚወስድበት ነው። ቀንና ሰዓቱን ከ**እግዚአብሔር** በቀር የሚያውቅ እንደሌለ **ጌታ ኢየሱስ** ነግሮናል በወንጌሉ፥ ነገር ግን ሁል ጊዜ ተዘጋጅተን እንኖር ዘንድና በጸሎት እየተጋን በቅድስና እየተፋቀርን በ**መንፈስ ቅዱስ** መሪነት እንደ ቅዱስ ቃሉ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ እንድናገለግለው፣ ተዘጋጅተን እንድንጠብቀውና ሁል ጊዜ ተዘጋጅተን እንድንኖር በፍቅር አዞናል። በንስሐ አሁኑኑ ወደ እርሱ እንመለስ፣ የልጁም **የኢየሱስ ክርስቶስ ደም** ከኃጢአት ያነፃናል፥ እለት እለትም በጌታችን ክርስቶስ ኢየሱስ ተጣብቀን መልካም ፍሬ እያፈራን እንኑር በፍቅር እንደቃሉ እንጠብቀውም፤ መምጫው ሲቀርብም የሚሆኑትን ምልክቶችንም ነግሮናል፥ እነዛም ምልክቶች መሆን ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል አሁንም እየሆኑ ናቸው። **ጌታ** በየትኛዋም ደቂቃ ሊመጣ ይችላልና ተዘጋጅተን በትሕትና ለቃሉ እየታዘዝን፣ ቃሉንም እያደረግን እንጠብቀው፣ ራሳችንን ክደን እለት እለት መስቀሉን ተሸክመን እንከተለው፣ በመንፈስ እንመላለስ፣ ሥጋን ከመጥፎ መሻቱና ምኞቱ ጋር እንስቀል፤ **መንፈስ ቅዱስ** ሆይ እርዳን በ**ኢየሱስ ክርስቶስ ኃያልና ቅዱስ ፍቅር ስም**። ሃሌ ሉያ አሜን። የጌታችንና የመድኃኒታችን የአምላካችን **የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** ወንጌል በማቴዎስ 24:36-51 / 25:1-13፣ **እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ** በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አንደበት እንደተናገረው በመጀመሪያይቱ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 4:16-18፣ ወደ ኤፌሶን 5:27) እርሱ መነጠቅን አላሳየኝም፣ ነገር ግን እርሱ ከመነጠቅ (ከንጥቀት) በፊት የሚሆኑ (ሊሆኑ ያሉ) ነገሮችን አሳይቶኛል። በእያንዳንዱ ቀን እኛ እየቀረብን እና እየቀረብን ነው። እኔም ይህን እነግራችኋለሁ **ንጥቀት ቀርቧል!** ራሳችሁን፣ ህይወታችሁን መፈተሽ አለባችሁ፣ እና ራሳችሁንም እንዲህ ጠይቁ:- *"ከ**ጌታ** ጋር ለመሄድ ዝግጁ ነኝ?"* **ጌታ** ይህን አሳይቶኛል፥ ነገር ግን እርሱ ለማንኛውም ሰው እንዳልናገር፥ ግን እንድጠብቅና መጨረሻው ቅርብ እንደሆነ እንዳይ ነግሮኛል፣ **እግዚአብሔር**ን መፈተን አልፈልግም፣ ለዛ ነው ያየኹትን ልነግራችሁ ያልፈለግሁት። ነገር ግን መነጠቅ (ንጥቀት) ቅርብ እንደሆነ እየነገርኋችሁና እያስጠነቀቅኋችሁ ነው።

[ትንቢተ ኢዩኤል 2:28]ን አነባለሁ፣ ከመጨረሻዎቹ ትንቢቶች አንዱ ነው፥ ሁሉም ተፈጽመዋል። ሳይፈጸም የነበረው ብቸኛው ትንቢት ይህ ነው፥ እና አሁን እነግራችኋለሁ ይህ ትንቢት እየተፈጸመ ነው። ብዙ ወጣት ሰዎች እየተነሡና **የእግዚአብሔርን ቃል** እየሰበኩ ነው። ሰይጣን ከወጣት ሰዎች የተውጣጣ የጦር ሠራዊት መሥራት ይፈልጋል፥ ነገር ግን **ጌታ** የበለጠ ኃይለኛ ነው። የእውነት **ጌታ**ን ከተቀበልህ (ከተቀበልሽ) እና እርሱን ማገልገል ከፈለግህ (ከፈለግሽ)፥ ሰይጣንን ለማሸነፍ እርሱ ጥንካሬውን ይሰጥሀል (ይሰጥሻል)፥ ስለዚህ ልክ እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳዘዘው በዓለም ዙሪያ **ቃሉን** መስበክ ትችላለህ (ትቺያለሽ)።

እኔ አንድ ተልዕኮ እንዳለኝ ነገረኝ፥ ይህም ተልዕኮ ስለ ራዕዬ ለሁሉም ወጣት ሰዎች መንገር ነው። ይህን ለማድረግ ባልፈልግ እንኳ፥ ይህ **ጌታ** የሰጠኝ ትእዛዝ ነው፣ እኔም እፈፅመዋለሁ።

ወደ ሰውነቴ ስመለስ፥ ተነሣሁና ራሴን በሆስፒታል ውስጥ አገኘሁት። እኔም ዙሪያውን ተመለከትሁ እና በክንዶቼ ላይ መርፌዎችን፣ ልቤን የሚመረምሩ ነገሮችን፣ ቲዩቦችን (ማስተላለፊያ ቀጫጭን ጎማዎችን) ተመለከትሁ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወላጆቼ ወደ ሆስፒታሉ መጥተው ገቡ እኔም ማልቀስ ጀመርሁ። እነርሱ በጣም የተቆጡ ይመስላሉ፥ **ጌታ** ግን ሁሉንም እንድነግራቸው ነገረኝ፥ የነገረኝንም አደረግሁ። እኔ ሁሉንም ነገርኋቸው።

ነርሷ ወደ ውስጥ ስትገባ፥ እነርሱ (ዶክተሮቹ፣ ነርሶቹ) ስለ እኔ እጅግ በጣም ተጨንቀው እንደነበረ ነገረችን። እሄድና (እሞትና) ከዛ ተመልሼ እንደምመጣ፥ ከዛም እሄድና ተመልሼ እመጣ እንደነበር ተናገረች። አዕምሬዬን የሳትሁ እሆን ነበር ከዛ በድጋሜ ንቁ

እሆናለሁ። ይህ ሦስት ጊዜያት ሆነ። በእነዚያ ጊዜያት አንዴ፣ እኔ ለመመለስ አልፈለግሁም ነበር፥ እነርሱም ስለ እኔ ተጨንቀው እንደነበረ ተናገሩ።

አረፋ ከአፌ ይወጣ እንደነበር፥ እኔም እነርሱ ሊረዱት እንኳ ያልቻሉትን ቃላት እለፈልፍ እንደነበር እነርሱ በድጋሜ ተናገሩ።

በድጋሜ በዛ ምሽት፥ እናቴ መጥፎ ህልሞች ነበሯት (መጥፎ ህልሞች እያለመች ነበር)። አብሬው የምተኛው ትንሽዬ ውሻ ወደ ወላጆቼ ክፍል ሄደና የእናቴን ክንድ ቧጨረና ሊቀሰቅሳት (ሊያስነሣት) ሞከረ። እርሷ እንደተነሣች ወደ ክፍሌ ተራመደች፥ እና ትራሶች ተቀምጠው አየች። እኔ እዛ ያለሁ ስለመሰላት እንደዛ አሰበችና ተመልሳ ወደ ክፍሏ ተራመደች። ከዛ የፖሊስ መብራቶችን ከመስኮቱ ውጭ ተመለከተች። በመስኮቱ በኩል ወደ ውጭ ስትመለከት፥ ፖሊሶች ወደ ቤታችን ሲራመዱ ስለተመለከተች አባቴን ቀሰቀሰችው። ስለ እኔ ለማወቅ (ለመጠየቅ) ወደ ፖሊስ ዲፓርትመንት እንዲደውሉ ፖሊስ ነገራቸው። ከመጠን በላይ ሰክሬ (ተመርዤ) በሆስፒታል ውስጥ እንዳለሁ ወላጆቼ አወቁ። በዛ ጊዜ፥ **ጌታ** ለአባቴ ተናገረና ሁሉም ነገር በእጆቹ ውስጥ ስላለ እንዳይጨነቅ ነገረው፥ ስለዚህ አባቴ አልተጨነቀም። በሆስፒታል ውስጥ ሦስት ቀናት አሳለፍሁ።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ከመርማሪዎቹ ጋር ተነጋገርን፥ እነርሱም ስለዛ ምሽት ነገሩን። ከእርሷ ጋር የነበርሁት ሌላኛዋ ሴት፥ እርሷም እንደኔው ትወጣለች ተብሎ አልታሰበም ነበር፥ እና አባቷ በጣም ተጨነቀ። እርሱ ዙሪያውን እየነዳ ሊፈልጋት ወጣ፥ ነገር ግን ሊያገኛት አልቻለም። ስለዚህ ወደ ፓሊስ ጣቢያ (ዲፓርትመንት) ሄደ፥ ፓሊስም ጓደኛዬ ይነዳው የነበረውን የመኪና አይነት ለሁሉም በመኪያ እየተዟዙ ለሚቃኙ ፖሊሶች አስታወቀ። በአረፍት ላይ የነበረ አንድ የፓሊስ መኮንን ከመንገዱ ባሻገር በአንድ የመኪና መሸጫ ቦታ ላይ ነበር። እርሱ ጥቅም ላይ የዋለ መኪና ሊገዛ እየተመለከተ ነበር። እርሱ ቃኘት አደረገ እና የጓደኛዬን መኪና ስላየ ፓሊስ ጠራ።

ፖሊስ ለመመርመር ሲሄድ የጓደኛዬ መኪና በሌላ ቦታ ላይ ቆማ ነበር፥ ስለዚህ እሷ የት እንደነበረች አላወቁም። እኛ በሁለተኛ ፎቅ ጥግ ላይ ባለው ክፍል ውስጥ ነበርን። ፖሊስ ከዛ ክፍል ለመጀመር ፈለገ፥ እና እያንዳንዱን ክፍል ለማጣራት ውጭ ያለችውን መኪያ ባለቤት እየጠየቀ ወረደ። እነርሱ ልጅቷን እየፈለጉ አልነበረም፣ እነርሱ ባለቤቱን ብቻ እየፈለጉ ነበር።

እነርሱ በራችንን ሲያንኳኩ፥ እነሱ በሩን ከፈቱ እና እኔን መሬት ላይ አዩኝ። ከዛ ግን እነርሱ ሄዱ። ጓደኞቼ ተብዬዎች ፖሊስ ለመልካም ሄደ ብለው አሰቡ፥ ነገር ግን በእርግጥ አምቡላንስ ለማምጣት ነው እነርሱ የሄዱት። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሌላ ፖሊስ እዛ ምን እየሆነ እንደሆነ ለማየት ወደ ላይ እዛ መጣ። እነርሱ በሩን ሲከፍቱ፥ በዛ ጊዜ፥ ጓደኛዬ፥ እያወራሁለት የነበረው፣ የተማመንኩት፣ እሱ እኔን ሊደፍረኝ ነበር። **ጌታ** ግን ያን ሁሉ ለማስቆም ፖሊሱን ተጠቀመ፥ እና እነሱ እኔ ላይ አንዳች አላደረጉም። ለዛ ነው **ጌታ**ን የማመሰግነው፥ ምክንያቱም እርሱ በኔ ላይ ምሕረት አድርጓል።

ደግሞም የወላጆቼ ጸሎት፥ ወላጆች ለእናንተ እየተናገርሁ ነው። ለልጃችሁ መጸለይ በፍፁም አታቁሙ። እነርሱ ከ**ጌታ** ጋር እየተራመዱ ካልሆነ፥ ለእነርሱ መጸለይ ቀጥሉ፥ በፍፁም አታቁሙ። ወላጆቼ በፍፁም አላቆሙም፥ እና አሁን እኔ የት እንዳለሁ ተመልከቱ፥ **የእግዚአብሔርን ቃል** እየሰበክሁ፣ **ጌታ**ን ለማገልገል እንዲመጡ ወጣት ሰዎችን እየነገርሁ፥ ምክንያቱም እርሱን ይፈልጉታል (እርሱ ያስፈልጋቸዋል)።

እኔም ለሁሉም ወጣት ሰዎች መልእክት መስጠት እፈልጋለሁ፥ ስለ ራሳችሁ እንድታስቡ፣ ራሳችሁን እንድትመረምሩ እፈልጋለሁ። አስቡ፥ ማንኛውም ሰው ስለ እኔ ስላለው ለምንድን ነው የምጨነቀው። ሌሎች ሰዎች ስለ እኔ ሊሉት ስለሚችሉት አስብ ነበር፥ አሁን ግን ለኔ እንደማይጠነቀቁ እንኳ ተረዳሁ። **ጌታ** በቀጥታ ከፊት ለፊቴ ሲሆን እነሱ እዛ አይሆኑም። ከ**ጌታ** ፊት ሳለሁ አስታውሳለሁ፥ ጓደኛዬ ሊረዳኝ እዛ አልነበረም፣ ቤተሰዎቼ ሊረዱኝ እዛ አልነበሩም፣ ፓስተሬ፣ ቤተ ክርስትያን እኔን ለመርዳት እዛ አልነበሩም። እኔ እዛ በራሴ (ራሴን ችዬ) ነበርሁ፥ እና ራሴን መከላከል ነበረብኝ። ከፊቱ ሆናችሁ መዋሸት አትችሉም፥ ምክንያቱም **እርሱ በጣም ቅዱስ ነው**። እና እዛ ሳለሁ እኔ እዛ እገባለሁ የሚል ስሜት አልተሰማኝም፥ ምክንያቱም እኔ በኃጢአት ውስጥ ነበርሁ እና በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ሁሉም ቅዱስ ነው።

**ጌታ ኢየሱስ**ን ካልተቀበላችሁት ዛሬ እንድትቀበሉት ዛሬ እነግራችኋለሁ። ይህ በህይወታችሁ ሙሉ ከሁሉም የሚበልጥ እጅግ በጣም ጠቃሚ ውሳኔ ነው። ይህን ሁሉ የምነግራችሁ ወደ መንግሥተ ሰማይ ላስፈራራችሁ አይደለም፥ ነገር ግን እርሱ (**ቅዱስ አዳኝ ጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ**) ለእኛ ያለውን **ምሕረቱን፣ ፍቅሩን** ማየት እንድትችሉ ነው። እርሱ **እግዚአብሔር አብ**፣ ለእኛ እንዲሞትልን **የእርሱን ልጅ** ላከ። ስለዚህ ፈሥሦ የነበረው እያንዳንዱ ጥቂት ነጠብጣብ ደም (**የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ**)

ሁሉንም ኃጢአታችንን ይቅር ይላል። **ጌታ**ን ለመቀበል ከፈለጋችሁ፥ ይህ በሕይወታችሁ ውስጥ ከሁሉም የሚበልጥ እጅግ በጣም ጠቃሚው ውሳኔ ነው። ወደ **ጌታ** ኑ፥ ማንኛውም ሰው ስለ እናንተ ስለሚለው አትጨነቁ።

**ጌታ**ን ለማገልገል ከፈለጋችሁ በፍጹም ልባችሁ አድርጉት፣ በአፋችሁ ብቻ አትበሉት፣ በልባችሁና በአዕምሮዋችሁ በሉት።

ስለ ወደፊቱ አትጨነቁ፥ ስለዛሬ ተጨነቁ፥ መቼ እንደምትሞቱ በፍፁም አታውቁም። እኔ 15 ዓመቴ ብቻ ነው እና በአዕምሮዬ በ15 ዓመቴ ልሞት እንደነበረ በፍፁም አስቤ አላውቅም፥ በፍጹም።

እናንተ ግን ስለዛ ማሰብ ያስፈልጋችኋል። ሕይወቴ የእኔ አይደለም፣ ሕይወታችሁ የእናንተ አይደለም፣ እኛ ሕይወታችንን እየተበደርን ነው፥ የእኛ ሕይወት ለ**እግዚአብሔር** የሚገባ ነው (ይገባል)። እኛ ባለመጠንቀቅ፣ ወደ ዓለም ውስጥ በመሄድ፣ የዓለምን ነገሮች በማድረግ ይህን እንጎዳለን። ዓለም የሚያቀርበው ብዙ ነገሮች አለው። ነገር ግን **እግዚአብሔር** የሚያቀርበው የበለጠ ነገሮች እንኳ እንዳሉት አስታውሱ። ዓለም ሲኦልና ሞት አለው፥ **እግዚአብሔር** ግን የዘላለም ሕይወት አለው። የዘላለም ሕይወት ለዘላለም ነው።

አሁን **ጌታ**ን ለመቀበል ከፈለጋችሁ፣ ራሳችሁን ዝቅ (ጎንበስ) እንድታደርጉና ዐይናችሁን እንድትዘጉ እፈልጋለሁ፣ “***ጌታ እግዚአብሔር*** *ሆይ፥* ***በኢየሱስ ስም*** *ወደ አንተ መጥቻለሁ፥ ኦ* ***ጌታዬ እግዚአብሔር*** *በዚህ ጊዜ አንተን እንደ አዳኜ ልቀበልህ እፈልጋለሁ፣ አንተ ወደ ሕይወቴ እንድትመጣ እፈልጋለሁ። እህት ስለ ምስክርነትዋ ሲኦል እውን እንደሆነ፣ እርሷም እዛ እንደነበረች እንዳለችው።* ***ጌታ እግዚአብሔር*** *ሆይ፥ እኔ እዛ መሄድ አልፈልግም፥ እዛ ስለመሄድ እንኳ ማሰብ አልፈልግም።* ***ጌታ እግዚአብሔር*** *ሆይ፥ የፈጸምኳቸውን ሁሉንም ኃጢአቶቼን ይቅር እንድትለኝ እጠይቅሃለሁ። ስላደረግሁት ማንኛውም ነገር ይቅር በለኝ። የኔ* ***ጌታ እግዚአብሔር*** *ሆይ፥ እያንዳንዷን ትንሽ ድብቅ ኃጢአት ላንተ ገልጫለሁ፥ ስለዚህ ለዛ ሁሉ እባክህን ይቅር በለኝ።* ***ጌታ እግዚአብሔር*** *ሆይ በመስቀል ላይ እንደሞትክ እና ከሙታን እንደተነሣህ አምናለሁ። አንተ ወደ ልቤ ውስጥ እንደምትመጣና በልቤ ውስጥ እንደምትነግሥ፣ በልቤም ውስጥ እንደምትሆን አምናለሁ። እኔ* ***ቃልህን*** *አነባለሁ፣ እና በ****ቃልህ*** *ውስጥ የበለጠ እሆናለሁ።* ***ጌታ እግዚአብሔር*** *ሆይ፥ አንተ በቤተ ክርስቲያን እንዳለህ ስለማውቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ። ሁለት ወይም ሦስት በአንድ ላይ ሲሰባሰቡ አንተ እዛ እንዳለህ ተናግረሃል። የኔ* ***ጌታ እግዚአብሔር*** *ሆይ አንተ ያለህበት መሆን እፈልጋለሁ። ይህን ሁሉ* ***በኢየሱስ ስም*** *ጸልያለሁ፥ አሜን።*”

ይህን ጸሎት ከጸለያችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ውስጥ እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት እፈልጋለሁ። አሁን በዓለም ዙሪያ ሁሉ ወንድሞችና እህቶች አሏችሁ። ከምታደርጓቸው ውሳኔዎች ሁሉ ይህ ከሁሉም በላይ እጅግ በጣም ጠቃሚ ውሳኔ ስለሆነ አትጣሉት። ወደ ዓለም ውስጥ አትመለሱ (ተመልሳችሁ አትሂዱ)። ዓለም ወደ ሞት ይመራል፥ **እግዚአብሔር** ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይመራል። በእያንዳንዷ ጊዜ ልክ የመጨረሻ ቀን እንደሆነ አድርጋችሁና የሕይወታችሁ የመጨረሻ ሰዓት እንደሆነ አድርጋችሁ መኖር ያስፈልጋችኋል። ይህ ምስክርነት ልባችሁን ከነካችሁ፥ ጓደኞቻችሁም ደግሞ **እግዚአብሔር**ን ወደ ልባቸው ውስጥ እንዲቀበሉት ምስክርነቱን ለጓደኛ ስጡት። ይህ የመጨረሻ ሰዓታችሁ ሊሆን ስለሚችል፥ ይህ ሰዓት እንዲያልፍ አታድርጉ።

# Hell is real, I went there!

by ***Jennifer Perez***

# ሲኦል እውን ናት፥ እኔ እዛ ሄጄ ነበር!

በ ***ጄኒፈር ፔሬዝ***

የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ የእግዚአብሔር አብ ቃልና ልጅ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ቅዱስ እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የልጁን የቶማስ ቶሙከዳህታን አካል ተጠቅሞ ተረጎመው። hithomasgetachew@gmail.com